መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
አቅራቢዎች



# ሁለት ጊዜ
# የኖረችው ልጅ

ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Janie Forest

ያሻሽለው (አሻሽሎ የጻፈው): Ruth Klassen

የተተረጎመው: Henok Estifanos

አዘጋጂ: Bible for Children
www.M1914.org

©2020 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፥- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።



ኢያኢሮስ እግዚአብሔርን የሚያመልክ እና ለሌሎች የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተምር የአይሁድ ሐይማኖት መሪ ነው፡፡ አንድ ቀን፤ ከባድ የሆነ ችግር ወደ ኢያኢሮስ መጣ፡፡ በጣም የሚወዳት የአስራ ሁለት ዓመት ልጁ በጠና ታመመች፡፡

ማንም ሰው ሊረዳት የሚችል አይመስልም ነበር፡፡ በጣም ከባድ የሆነ በሽታ ነበር፡፡ኢያኢሮስ ልጁ እንደምትሞት አወቀ፡፡



ኢያኢሮስን ልጅ ሊረዳ የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ነው።ኢያኢሮስ ኢየሱስን መፈለግ እና ወደ ቤቱ ለማምጣት ጀመረ።



የኢያኢሮስ የሐይማኖት ጓደኞች ኢየሱስ እንደሆነ አላረጋገጡለትም፡፡ ነገር ግን ኢያኢሮስ ግድ አልሰጠውም፡፡ ልጁ ከመሞቷ





ኢያኢሮስ
ኢየሱስን በሰው
ተከቦ አገኘው፡፡
በኢየሱስ
ፊት ወድቆ
ሰገደ፡፡ "ልጄ
ልትሞትብኝ
ነው፤" ያዘነው
ሰው ለመነው፡፡



መጥተህ እጅህን
ጫንባት፤እሷም
ትፈወሳለች፤
እናም
በህይወት
ትኖራለች“
አለው፡፡



ኢየሱስም ከኢያኢሮስ ጋር ሔደ። ነገር ግን ከተጨኛ ነቀው ህዝብ የተነሳ በፍጥነት መሄድ አልቻሉም። አንዲት ሴት ለአስራ ሁለት አመት ታማ ነበር። ወደ ሁሉም ዶክተሮች ሄዳ ቢሆንም ምንም እርዳታ ልታገኝ አልቻለችም (እናም በርካታ ገንዘብ አጥፍታ ነበር)። ኦ እንዴት ኢየሱስን ማግኘት ትፈልግ!



ሴቲቱ ምን
አደረገች? "የልብሱን ጫፍ ብነካ
እንኳን እፈወሳለሁ፤" ብላ ለራሷ
ተናገረች፡፡ወደ ኢየሱስ ተጠጋች፡፡
ከዚያም እጆቿን ዘረጋች እና
የኢየሱስን ቀሚስ ነካች፡፡



ታዕምር ነው! ታዕምር ነው! ሴቲቱ
ተፈወሰች፡፡ ወዲያውኑ! ሙሉ
በሙሉ! ደህና ፤ከዚያም ብርቱ እና
ሙሉ እንደሆነች አወቀች፡፡ነገር ግን
አንድ ድምጽ ተናገረ፡፡"የነካኝ ማን
ነው?" ብሎ ኢየሱስ ጠየቀ፡፡በርካታ
ህዝብ ነክቶታል፡፡ ነገር ግን
የተፈወሰችው ሴት ስለ እርሷ
እየተናገረ እንደሆነ አወቀች፡፡
እየተንቀጠቀጠች፤ታሪኳን
ሁሉ ነገረችው፡፡

ወዲያውም፤የኢያኢሮስ አገልጋዮች መጡ።
ከመናገራቸው በፊት ፊታቸው የሐዘን ወሬ ይዘው
እንደመጡ ይናገራል።
"ልጅህ ሞታለች!" ብለው
ለኢያኢሮስ ነገሩት።
ሞታለች! በጣም
ረፍዷል።



ምናልባት፤ ያቺ ሴት የሚያስረፈድ ነገሮች ባይኖሯት...
ምናልባት... ሞተች! የኢያኢሮስ ውድ ልጅ ሄደች፡፡



ኢየሱስ በሰማ ጊዜ፤"እመን
እንጂ አትፍራ፤እሷ ደህና
ትሆናለች" አለው፡፡
ኢየሱስን በእውነት
ማመን ለኢያኢሮስ
ምን ያህል ከባድ ነው፡፡
ልጁ ሞታለችና፡፡

በቤት ሁሉም ሰው ለልጅቷ ያለቅስ እና ሀዘን ተቀምጦ ነበር። "ልጅቷ ተኝታለች እንጂ አልሞተችም፤" ብሎ ኢየሱስ ነገራቸው። እነርሱም ሳቁበት። ልጅቷ እንደሞተች ያውቃሉና።



ኢየሱስ ሁሉንም ሰው ከቤት አስወጣቸው፤ልጅቷን እጆቿን ይዞ "አንቺ ብላቴና፤ተነሺ" አላት። ኢያኢሮስ በዚያ ነበር።ባለቤቱም በዚያ ነበረች። ሦስቱም ደቀመዛሙርት በዚያ ነበሩ። ሁሉም የኢየሱስን ቃል ሰምተዋል። ትንሿ ልጅ ሰምታቸዋለችን?



የሞተችው ልጅ የኢየሱስን ትዕዛዝ ሰማች! መንፈሷ
ተመለሰ፤ወዲያውኑ
ተነሳች። ኢየሱስ
ከሞት አስነሳት።



የልጅቷ ወላጆች ተደነቁ፡፡ ኢየሱስ ለልጅቷ የምትበላውን ስጧት አላቸው፡፡ ምን ያህል ደስታ ይሰማቸዋል፤በኢየሱስ ምን ያህል ደስ ይላቸዋል፡፡ የእርሱ አስደናቂ የሆነ ፍቅር እና ኃይል ልጅቷን ከሞት ወደ ህይወት አመጣት፡፡



ሁለት ጊዜ የኖረችው ልጅ

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ማርቆስ 5, ሉቃስ 8

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

# መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን
ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን
በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር
እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው
ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና
ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሠጠት
እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት
እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ
በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን
እኛም በኢየሱስ አዳኝነት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር
እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል።
እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ
ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ
ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ
አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል
ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ
ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን
ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር
ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ
ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ
ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16